ሳምንታዊ ዜና (ሰኔ 14 ቀን 2000 ዓ. ም.)

**አንድ የወያኔ ጄኔራል በተቃዋሚነት ተጠርጥሮ በጡረታ ተባረረ፣ በወለጋ መስመር ወደ ጐንደር ከ60 በላይ ታንክ ተጓጓዘ፣ በጐንደር በተደረገው ውጊያ አንድ ከፍተኛ መኮንንን ጨምሮ በርካታ ወታደሮች ተገደሉ፣ በሀገሪቱ የረሀብተኛ ቁጥር እያሻቀበ መሆኑን አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ስጋታቸውን ገለፁ፣ ወያኔ ሀሰተኛ ዶላር በኮንቴነር አስገባ፣ ዘረፋ በሀገሪቱ እየተስፋፋ መሆኑ ታወቀ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሌላም ዝርዝር ያንብቡ ..................................................**

የወያኔ ቡድን ለስርዓቱ አደጋ ናቸው የሚላቸውን የራሱን ካድሬዎች በተለያየ ጊዜ ለእስርና ለሞት እየዳረገ የመጣ መሆኑ ተጋለጠ::

ሰሞኑን ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ እንደገለፀው ከሆነ ከበረሀ ጀምሮ አብሯቸው የመጣውን ብርጋዴየር ጀኔራል ሆሎ ዳዊ የተባለውን የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ያለ እድሜው በጡረታ እንዲወጣ በነመለስ ዜናዊ እንደተወሰነበት የቤተመንግስት ምንጮች ገልጸዋል::

በፖለቲካ አመለካከታቸው ከእኛጋር ያልወገኑ ናቸው በሚል በርካታ ከፍተኛ መኮንኖችን መርጠውና አስረው ለብዙ ወራት ያንገላቷቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮች በተለይ ብርጋዴየር ጄኔራል ሀሎ ዳዊ ከሁሉም በላይ እስርና ስቃይ በዝቶበት እንደነበረም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ይኸው መኮንን የወያኔ ቀኝ እጅ ሆኖ ከሽግግር መንግስቱ በፊት አሩሲ ክፍለ ጦር ተብሎ የሚጠራውን የጦር ክፍል ሲመራ የቆየ እንደነበርና በኋላም ሠራዊቱ ሲደራጅ የብርጋዴየር ጄኔራልነት ማዕረግ ተሰጥቶት የአንድ ክፍለ ጦር አዛዥ አድርገውት ሲሰራ በ1997 ዓ.ም በተደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ሁለት ጀኔራሎች መክዳት ጋር በተያያዘ ተጠርጥሮ ለእስር ከተዳረገ በኋላ በቅርቡ ተፈትቶ በጡረታ እንደተባረረ መንጮች ገልፀዋል::

ስለመብት ጥያቄ በከፍተኛ መኮንኖች ስብሰባ ላይ ከማንሳት ወደ ኋላ እንደማይል የገለፁት እነኚሁ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች በወያኔ ውስጥ በተፈጠረው ችግር የተነሳ በወቅቱ የሕወሓት ጄኔራሎች ከመለስ ጋር በመሆን በሌሎች ብሄር መኮንኖች ላይ የእስርና የማባረር እርምጃ መውሰዳቸውን ገልፀው የአየር ኃይል ዋና አዛዥ የነበረው ሜጀር ጄኔራል አለምሸት ደግፌ ከጥቂት ቀናት እስራት በኋላ ከስራው የተባረረ ሲሆን እነ ብርጋዴየር ጄኔራል ሀሎ ዳዊ ግን ለብዙ ወራት የታሰሩና የተለቀቁ መሆኑንም ጨምረው አስረድተዋል::

መከላከያ ውስጥ ተሀድሶ ያስፈልጋል ተብሎ በግምገማ የሠራዊቱ አባላትን እያንከራተቱ የቆዩት ወያኔዎች ከየአቅጣጫው ከየጦሩ ከተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የተገመቱ መኮንኖችን ከስራ ያባረሯቸው መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ ብርጋዴየር ጄኔራል ሀሎ ዳዊም የዚሁ ሰለባ መሆኑን ገልፀዋል::

በተለይም ብርጋዴየር ጄኔራል ከማል ገልቹ የተባለውን ጄኔራል ተከትሎ ሌላ አንድ ጄኔራል ከብዙ ወታደሮች ጋር ከድቶ የጠፋ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ብርጋዴየር ጄኔራል ሀሎ ዳዊ በአይነ ቁራኛ ሲጠበቅ እንደነበረ ያወሱት ምንጮቹ ጊዜ ተጠብቆ ለእስር ከዚያም ለጡረታ መዳረጉን አብራርተዋል።

በአሁን ሰዓት በሠራዊቱ ውስጥ የሕወሓት የበላይነት ነግሶ የአንድ ወገን ተደማጭነት ያለበት መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ ለስሙ ከተለያየ ብሔር የተቀላቀሉበት ቢሆንም ለማስመሰል ያህል ካልሆነ ወሳኞቹ ሕወሓቶች መሆናቸውን አስረድተው በተለይም በቅርቡ ከምስራቅ እዝ አዛዥነት ያነሱት ሜጀር ጄኔራል ባጫ ደበሌ አንድ መምሪያ ውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገ ሲሆን፣ ለሀገሪቱ ሁለተኛ ሰው ነው የተባለው የአማራ ብሄር ተወላጅ ሌተናል ጄኔራል አበባው ታደሰ ለማስመሰል ማዕረጉ ተሰጠው እንጂ በሚያሳፍርና በሚያሳዝን ሁኔታ የአንድ እዝ አዛዥ አድርገው መልሰው ማስቀመጣቸው ታውቋል።

ለብዙ ጊዜ የመከላከያ የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቶ ለትምህርት ወደ ውጭ ደርሶ ከመጣ በኋላ የማዕከላዊ እዝ አዛዥ፣ አድርገው ያባረሩት ሲሆን፣ በኋላም ማዕረግ ሲሰጥ የሌተናል ጄኔራልነት ከሳሞራ የኑስ ቀጥሎ ያገኘ መኮንን ሲሆን በወቅቱ ወደ መከላከያ ዋና መምሪያ አምጥተው የነበረ ቢሆንም በአሁን ሰዓት ግን የአንድ ተራ እዝ አዛዥ አድርገው ወደ ሽሬ ያባረሩት መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

የብሔር ስብጥር አለ ለማሰኘት ብቻ ለሆዳቸው ያደሩ ጥቂት ግለሰቦች የከፍተኛ መኮንንነት ማዕረግ እየተሰጣቸው እንደ እቃ እንዲቀመጡ የተደረገ ቢሆንም በአሁን ሰዓት ውስጥ ውስጡን በሰራዊቱ ውስጥ አንዳንድ ጥያቄዎች እየተነሱ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

በጉንደርና በጋምቤላ በኩል ወያኔ መሬት ቆርሶ ለሱዳን ከሰጠ በኋላ በርካታ የሠራዊቱ አባላት ጥያቄ እያነሱ እንደነበርና በአሁን ሰዓት በየክፍሉ ግምገማ መጀመሩ ስርዓቱ የሠራውን በደልና ግፍ ለመሸፈን ሲል ሠራዊቱ አንገቱን እንዲደፋ ለማድረግ ታስቦ የተደረገ መሆኑንም አስረድተዋል።ከግምገማ በኋላ በርካታ መኮንኖችና ወታደሮች የአመለካከት ችግር አለባቸው በሚል እንደሚባረሩ ይጠበቃል ሲሉም ምንጮቹ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል።

የወያኔው ቡድን ለሱዳን ከጉንደርና ከጋምቤላ በኩል መሬት ቆርሶ መስጠቱን ተከትሎ በጉንደር ውስጥ ከፍተኛ ውጊያ እየተካሄደ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለጠ።

ከግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በወያኔ ሠራዊት እና በተቃዋሚ ታጣቂ ድርጅቶች መካከል ውጊያ የተጀመረ ሲሆን፣ በወያኔ ድርጊት የተበሳጨው የአርማጭሆ እና የመተማ ሕዝብም ወደ ትግሉ እየተቀላቀለ መሆኑ ተገልጿል።
ወያኔ ሕዝብን ሳያማክርና ሳያናግር በምስጢር የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለሱዳን ከሰጠ በኋላ በተከፈተበት ውጊያ ግራ ተጋብቶ አንዴ ከሕዝብ ጋር እነጋገራለሁ አልተቋጨም ሌላ ጊዜ እኛ ምንም አይነት ስምምነት አላደረግንም እያለ ቢዘላብድም መሬታችን ለባዕድ ተቆርሶ አይሰጥም በማለት በውጊያ

እያጣደፉት ሲሆን እስከ ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በርካታ ቁስለኞችን ወደ ባህርዳር በድብቅ እያጓጓዘ መሆኑ ተገልጿል::

በሕዝብና በሀገር ላይ ከፍተኛ ክህደትና በደል የፈፀመው የገንዘብ ፍቅር የተጠናተው ወያኔ በተከፈተበት ድንገተኛ ጥቃት በመደናገጥ ከባድ መሣሪያዎችንና ግዙፍ ጦር ወደ አካባቢው እያስጠጋ ሲሆን በአየር ድብደባ ለመፈፀም ሙከራ ቢያደርግም በአካባቢ ባለው ደመና አየር ፀባይ ምክንያት ሂሊኮፕተሮችም ሆነ ጀቶች ለመብረር በመቸገራቸው ለጊዜው ለመጠቀም አለመቻሉን የደረሰን ዘገባ ገልፆ በአሁን ሰዓት በሠራዊቱም መሀከል የሞራል ልሽቀት በመድረሱ የተነሳ በወያኔ ላይ ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ኪሣራ እየደረሰበት መሆኑን ዘገባው አስረድቷል::

በወያኔ ድርጊት የተቆጣው የጐንደር ሕዝብ መሬታችን እስኪመለስ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ድረስ እንዋጋለን ብለው ከሱዳን ጋር የጀመሩትን ግብግብ በመተው የጦር አለቃ እየመረጡ ዱር ቤቴ ብለው ከወያኔ ጋር ውጊያ የጀመሩ ሲሆን በተመሳሳይም የወያኔ ተቃዋሚ ታጣቂ ኃይልም ጥቃት ሰንዝሮ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰበት መሆኑን ዘገባው አስረድቷል::

ይህንንም ተከትሎ በጐንደር ገጠር ውስጥ የወያኔ ካድሬዎች እየተዘዋወሩ «እስከአሁን ከሱዳን መንግስት ጋር በፍፁም ድርድር አልተደረገም:: መሬት ቆርሶ ተሰጠ ብለው የሚያናፍሱት የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው» እያሉ ለማታለል ቢሞክሩም ሕዝቡ በፊት ከነበረው በላይ በመብገኑ አንዳንዶቹን የወያኔ ካድሬዎች ከግንድ ጋር አስሮ ገርፎ የለቀቃቸው መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

ግራ የተጋባው ወያኔ ዛሬ ሌላ ነገር ነገም ሌላ እየዘላበደ ቢገኝም ሕዝቡ ግን መሬቱ ተቆርሶ ለባዕድ በመሰጠቱ ምክንያት በጣም አርሮ ያለ ከመሆኑም በላይ እትብቱ ከተቀበረበት ቀዬ እንዲነቀል ተደርጓል::

ህዝብንና ሀገርን ንቆ እንዳሻው እንደ ወጠጤ ፍየል አራምባና ቆቦ እየረገጠ የሚጓዘው ወያኔ በጐንደር እና በጋምቤላ መሬት ቆርሶ መሸጡ ሳያንሰው የታሰሩ ዜጐችን አንድም የታሰረ የለም የተፈናቀለ የለም እያለ በመሪው በመለስ ዜናዊ አማካኝነት መግለፁ ያሳርራል፣ ያበግናል ያሉት የሀገሪቷ ሕዝቦች ይህንን የእሾህ አሜኬላ የሆነ ቡድን በሕብረት ልንታገለው ይገባል ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው እየገለፁ ይገኛሉ::

መሬት ቆርሶ ሲሰጥ በድብቅ፣ ረሀቡ ሲከሰት ደብቆ ይዞ ምንም ድርቅ የለም ሲል፣ የኑሮ ውድነት የሀገሪቷን ህዝቦች እግር ከወርች አስሮ አላላውስ ስላለው እኛ ያመጣነው የኢኮኖሚ እድገት ነው እያሉ እያሾፉ የሚያደርጉት ሁሉ ህዝብን ንቀው ምን ታመጣላችሁ? ማለታቸው ነው ያሉት አንድ የህግ ባለሙያ ተወደደም ተጠላ ለወያኔ የኃይል እርምጃ መጠቀም ወሳኝ ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል::

በሀገሪቷ ጠኔ ጥሏቸው በተኙበት የሞቱትን ዜጐች እያየና እየተመለከተ ፈፅሞ ረሀብ በሀገሪቷ የለም ይህንን የሚያስወሩት ጥቅመኞች ናቸው እያለ የወያኔ ቡድን መለፈፉ ሳያንሰው መሬት ቆርሶ ከ1600

ኪ.ሜ በላይ ስፋት ያለውን ለም የሀገራችንን ምድር መሸጡ የሚያንገበግብ ነው ያሉት አንድ አባት አሁንም ገና ያልተጠናቀቀ ሴራ ስላለው ይህንን አረመኔ ቡድን ልንነቅለው ይገባል ሲሉ በንዴትና በብስጭት እየገለፁ ይገኛሉ፡፡

ወያኔ በጐንደርና በጋምቤላ በኩል መሬት ቆርሶ ከሰጠ በኋላ በአፄ ሚኒልክ ጊዜ ሻለቃ ጐይን የተባለ የእንግሊዝ ወታደር ያሰመረው መስመርን የኃይለስላሴም ሆነ የደርግ መንግስታት ስምምነት የደረሱበት ነው በማለት ከእውነት የራቀ ውሸት እየለፈፈ በሀገርና በህዝብ ላይ ደባ መፈፀሙ ሳያንሰው ድብቁን ሴራ ያጋለጡትን ዜጐች ታፍሰው እንዲታሰሩ ማድረጉ አንገብጋቢ ነው ሲሉ አንድ የሕግ ባለሙያ ይገልፃሉ፡፡

ወያኔ ከሕዝብ ይልቅ ገንዘብን፣ ከሀገር ይልቅ ጥቅምን ያስቀደመና ምንም የኢትዮጵያዊነት ስሜት በውስጡ ያልያዘ ቡድን ከመሆኑ የተነሳ ዛሬ በጐንደርና በጋምቤላ መሬት ቆርሶ መሸጡን በምስጢር ይዞ ከአንድ አመት በፊት የጨረሰ ሲሆን በቤንዚንና በገንዘብ ለውጦ ሀገርን ያህል ማስረከቡ ያንገበግበናል ወደፊት ግን በአለም አቀፉ ፍርድ ቤት የሱዳንን መንግስት ገትረን ሀቃችንን እንይዛለን ሲሉ እኚሁ የህግ ባለሙያ አበክረው ገልፀዋል፡፡

እራሱ ያወጣውን ሕገ መንግስት እራሱ ጥሶ ዳር ድንበራችንን ቆርሶ የሰጠ በመሆኑ ሁለቱ በድኖች ያደረጉትን ስምምነት በኀዳ ህዝብ ሳያውቀው በምስጢር የፈፀሙ በመሆኑ ያለምንም ማቅማማት ወያኔ ከተወገደ በኋላ በአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ህጋዊ መብታችንን እናስከብራለን ሲሉም አክለው ገልፀዋል፡፡

በጐንደር በኩል የተቃዋሚ ታጣቂ ኃይል ይንቀሳቀስበታል በሚል ፍራቻ እና በጥቅም መሬት ቆርሶ የሰጠው ወያኔ ወደፊት ሌላም የከፋ ወንጀል ሊፈፅም ይችላል ሲሉም ያላቸውን አስተያየት ገልፀዋል፡፡

የሚገርመው፣ የሚቆጨውና የሚያንገበግበው የሱዳን ወታደሮች በኢትዮጵያ ምድር እንዳሻቸው እየፈነጠዙ የዜጐቻችንን ሀብት ንብረት እያወደሙ፣ ከብቶቻቸውን እየነዱ ወስደው፣ በርካታ ዜጐቻችንን አፍሰው ሱዳን እስር ቤት ውስጥ አስረው እያንገላቷቸው እያለ አንድም የተፈናቀለ የለም አንድም የታሰረ የለም ብሎ መለስ ዜናዊ መግለጫ መስጠቱ ነው ብለዋል፡፡
ከ1 ወር በፊት በሱዳን የጦር ካምፕ ውስጥ ታስረው ከነበሩት መካከል ገንዘብ ያላቸው ጥቂቶቹ 2 ሺህ ብር ቅጣት ከፍለው የተለቀቁ ሲሆን ገንዘብ የሌላቸው ግን እስከአሁን በእስር ላይ መሆናቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆ በሱዳን የወያኔ አምባሳደር ተብየው ሆድ አደሩ አሊ አብዶ ስለ ዜገቻችን መታሰር ጣልቃ መግባት እንደማይቻል እና ሥልጣኑ እንደሌለው መግለፁ ከእነ መለስ ዜናዊ ጥብቅ ትዕዛዝ እንደተሰጠው የሚያመላክት መሆኑን የደረሰን ዘገባ ያስረዳል፡፡

በጐንደርና በጋምቤላ እንዲሁም በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ወያኔን በትጥቅ የሚፋለሙ ታጣቂ ኃይሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ ሲሆን ሰሞኑን በጐንደር በኩል ያለው እንቅስቃሴ ግን ከወትሮው ለየት ያለና የተጠናከረ በመሆኑ ከባድ መሣሪያ ወደ ስፍራው እያጓጓዘ መሆኑን ከአይን እማኞች የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት ማክሰኞ ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ከጦር ኃይሎች ፊት ለፊት ከቀድሞው የምድር ጦር መምሪያ ግቢ ከ60 በላይ ታንኮችን የጫኑ ሎቤዶች ወደ ዊንጌት በሚስደው ቀለበት መንገድ ሲጓጓዙ የታዩ መሆኑን የአይን እማኞች ገልፀዋል::

ከምሽቱ 4 ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊቱ 11 ሰዓት ድረስ ሕዝብ በተኛበትና አያይም በተባለበት በቀለበት መንገድ ወደ ወለጋ ተጭኖ የተጓጓዘ መሆኑን የገለፁት የአይን እማኞች ታንኮቹ ገና ምንም ያልሰሩ አዳዲስ መሆናቸውን አስረድተዋል::

በጉንደር እና በጋምቤላ የኢትዮጵያን መሬት ሸጠው ለሱዳን የሰጡት የወያኔ ባለሥልጣናት በሰሩት ሰህተት ከመፀፀት ይልቅ እየተንቀባረሩ የሕዝቡን አንጀት ባበገኑበት ወቅት የታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች እያርበደበዱት ፋታ በማሳጣታቸው የተነሳ በወለጋ መስመር ወደ ጉንደር ጋምቤላ ሌሊት ሌሊት ታንክና ሌሎችም የከባድ መሣሪያች እያጓጓዘ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

ለ17 ዓመታት በሕዝብ ላይ ሲቀልድና ሲያሾፍ የኖረው ወያኔ ሚሊኒየም እያለ በሚያቅራራበት ወቅት የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለባዕድ ከመሸጡም በላይ በቦታው ላይ ለዘመናት የኖሩት ኢትዮጵያውያንን የባዕድ ወታደሮች አስረው እያንገሏቷቸው መሆኑን እያወቀ ዝም ከማለቱም ባሻገር አንድም ኢትዮጵያዊ የታሰረ እና የተፈናቀለ የለም በማለት የንቀት መልስ እየሰጠ በዜጎች ላይ እየቀለደ ባለበት ወቅት ታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ከሕዝቡ ጋር በመተባበር ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱበት መሆኑን የገለፁት ምንጮች በተለይ ቁስለኞች እንዳይታዩ ሽራ በለበሱ መኪናዎች እየታሸጉ ወደ ባህርዳር በመግባት ላይ እንደሚገኙም ጨምረው ገልፀዋል::

በሜጀር ጄኔራል ስዩም ሀጉስ እየተመራ ያለው የምዕራብ ዕዝ ጦር ላይ ተደጋጋሚና ከፍተኛ ጥቃት በመድረሱ የድረሱልኝ ጥሪ በማቅረቡ የአየር ኃይል ምድብ ታዞለት በጄትና በሂሊኮፕተር እገዛ እንዲደረግለት የተፈቀደለት ከመሆኑም በተጨማሪ ከባድ መሣሪያ ከውጭ ሀገር አስመጥቶ ወደ ቦታው በማጓጓዝ ላይ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

ሕዝቡ በኑሮ ውድነት የተነሳ እህል መቅመስ ተስኖት ባለበት እና ከ11 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በረሀብ በተሰቃየበት በዚህ ወቅት ለነጋዴው የውጭ ምንዛሬ የለም እያለ በዶላር ከውጭ ሀገር ከባድ መሣሪያዎችን እያጓጓዘ መገኘቱ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ያሉት ምንጮች ከሁሉም በላይ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ ዜጎች እንደቅጠል እየረገፉ ባለበት በዚህ ወቀት በውድ ዋጋ እየሸመተ ማስገባቱ ያንገበግባል ሲሉ እነዚሁ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይገልፃሉ::

ከጉንደር አርማጭሆ በደረሰን ዘገባ መሠረት ሰሞኑን በተካሄደው ውጊያ በርካታ ወታደሮች ከመሞታቸውም በተጨማሪ ለጊዜው ስማቸው ያልታወቀ አንድ የሌተናል ኮሎኔል ማዕረግ ያለውና ሌላ አንድ ሻምበል እንደተገደለ አስረድተዋል::

በአሁን ሰዓት በወያኔና በሻዕቢያ ድንበር ላይ ከፍተኛ ፍጥጫ ያለ ከመሆኑም በላይ ከወትሮው በተለየ መልኩ ውጥረቱ ተባብሶ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ የተባለው ድርጅት ስጋቱን ገልጿል::

በሁለቱም ሀገራት ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ተከስቶ ዜጐቻቸው የእለት ጉርስ መቅመስ አቅቷቸው ባለበት ወቅት በተለይም የወያኔው ቡድን በየቀኑ ለወታደራዊ ተቋሙ የሚያወጣው ገንዘብ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን የሚገልፁት የመከላከያ ምንጮች ረሀብ እንደ ሰደድ እሳት በተስፋፋበት ወቅት እንኩዋን ወጪው የትየለሌ መሆኑን ለዜጐች አንዳችም ክብርና አዘኔታ የሌለው መሆኑን ያስረዳል ሲሉ በቁጭት ይገልፃሉ::

በሀገሪቱ በተከሰተው ረሀብ ምክንያት ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ዜጐች እየሞቱ መሆኑን ከተለያየ አካባቢ የሚደርሰን ዘገባ ገለፀ::

በተለይም ከአሩሲ፣ ከባሌ፣ ከደቡብ አርባ ምንጭ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ እንደገለፀው ከሆነ የረሀብተኛው ቁጥር እጅግ በየቀኑ እያሻቀበ ከመሆኑም በላይ በዚያ ሳቢያ የሚሞቱት ዜጐች ቁጥርም እያደገና እየጨመረ መምጣቱን ያስረዳል::

ወያኔ ረሀብ አልተከሰተም እያለ ደብቆ ቢዋሽም የአለም አቀፍ ድርጅቶች ተከታትለው ያለውን እውነታ በማጋለጣቸው የተነሳ ሀቁ ሊወጣ የቻለ ሲሆን በወቅቱ ወያኔ ደብቆት ባይሆን ኖሮ ችግሩ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ ላይደርስ ይችል ነበር ያለው ይኸው ዘገባ በአሁን ሰዓት አደገኛ ሁኔታ እንደተፈጠረም ገልጿል::

በሐረር በተለይ ዜጐች እያለቁ ሲሆን በሀገሪቷ ተከሰተ ከተባለው ከ1966 እና 1977 ዓ.ም በላይ በከፋ መልኩ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ወያኔ ግን ረሀብ የለም እያለ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጐች እስኪሞቱ ድረስ አንዳችም እርምጃ ያለመውሰዱ አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲልም ዘገባው አብራርቷል::

በአሁን ሰዓት የአለም ምግብ ድርጅት ወያኔን ተጠያቂ እያደረገው በመምጣቱ የተደናገጡት ባለሥልጣናት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የተባለውን መስሪያ ቤትና ኃላፊዎቹን መወንጀል መጀመራቸው ታውቋል::

ወትሮም እንደ ሸንኮራ መጥጦ መጣል የሚያውቅበት ወያኔ ለ17 ዓመታት ሲጠቀምበትና የገንዘብ መሰብሰቢያ አድርጐት የነበረውን አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲን «ዝርክርክ አሰራር ሲያደርግ ነበር፣ ለተራቡት ቀድሞ አላደረሰም» በማለት እያጣጣለው ከመሆኑም በተጨማሪ በቅርቡ በግብርናና በገጠር ልማት ሚኒስቴር ስር ሊካተት መሆኑ ታውቋል::

የአለም ህብረተሰብና መንግስት በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሀብ በአጭር ጊዜ የሆነ አይደለም በማለት ወያኔን እያጣደፉት ባለበት ወቅት ባለሥልጣናቱ ከተጠያቂነት ለማምለጥ በነስምኦን መቻሌ ላይ ጣታቸውን እየቀሰሩ ሲሆን በቅርቡም የአደጋ መከላከልና ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና በሚል በአዲስ መልክ እንዲዋቀር መደረጉን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጐች ለከፋ ረሀብ ተጋልጠው በሚገኙበት በዚህ ወቅት የአለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች እና ጋዜጠኞች ከእርዳታ በስተቀር ፎቶ ግራፍ እንዳያነሱ የሚከለክል ደብዳቤ ከወያኔው ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ መውጣቱን የሚኒስትር መስሪያ ቤት ምንጮች አጋለጡ።

ባለፈው ሳምንት ወጪ የተደረገው ይኸው ደብዳቤ የወረዳ ባለሥልጣናትን የሚያስጠነቅቅ ሲሆን አንድም የውጭ ሀገር ጋዜጠኛ ረሀብተኞቹን ፎቶ እንዳያነሳ እና ለጋሽ ድርጅቶች ሠራተኞችም ቢሆኑ ከልገሳ ባሻገር ምንም ፎቶ እንዳይቀርፁ የሚከለክል መሆኑን እና ይህ ሆኖ ቢገኝና አለም አቀፍ ሚዲያ ላይ ቢቀርብ ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያስረዳ ደብዳቤ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

ወያኔ ሆን ብሎ ሕዝቦች እንዲያልቁ በሩን ዘግቶ ከቆየ በኋላ ገመናው ቢወጣም አሁንም የበለጠ እንዳይጋለጥ በመፍራት ይህንን መሰል ትዕዛዝ መስጠቱ ለባለሥልጣናቱና ለራሳቸው ክብር ብቻ በማሰብ የፈፀሙት ድርጊት ነው የሚሉ በርካታ ዜጐች ናቸው።
በጦርነትና ወያኔ ባመጣው ጣጣ የዜጐች የኑሮ ደረጃ ከቀን ወደ ቀን እየወረደ በመጣበትና የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እየተንኮታኮተ ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ በኮንቴነር የሀሰተኛ ዶላር ብር አሳትሞ ማሰራጨቱ የብሔራዊ ባንክ ምንጮች ጠቆሙ።

በሀገሪቱ ውስጥ ምንም አይነት የውጭ ምንዛሬ የሌለ በመሆኑ ነጋዴዎች በተለይ አስመጪና ላኪዎች የውጭ ምንዛሬ ሲጠይቁ ከ3 ወር በፊት አታገኙም ከሌላ ውጭ ካለ ድርጅት መበደር ትችላላችሁ እያሉ በሚመልሱበት ወቅት ሰሞኑን የወደቀው የሀገሪቷ ኢኮኖሚ እንዲቀበርና ለመቼም ቢሆን እንዳይነሳ ለማድረግ የሀሰተኛ ዶላር ሀገር ውስጥ አስገብተው በወያኔ አባል ነጋዴዎች አማካኝነት የምንዛሬ ስራ እየሰሩ መሆኑን ምንጮች አጋልጠዋል።

ምንም ነገር ከመፈፀም ወደ ኋላ የማይለው ወያኔ ሰሞኑን ግራ በተጋባበት ወቅት ሀሰተኛ ዶላር አስገብቶ እያሰራጨ ከመሆኑም በተጨማሪ ፍፁም ከስራው ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ነገር ግን በየጊዜው ከውጭ ሀገር ሸቀጥና ልብስ የሚያመጡ ነጋዴዎችን በፈጠራ ክስ እያሰራቸው ሲሆን ከስታዲየም ዙሪያ ከመርካቶ እና ከሌሎችም አካባቢዎች 84 ነጋዴዎች መታሰራቸውንም ምንጮቹ ጠቁመዋል።

በአሁን ሰዓት ለነጋዴዎችም ሆነ ለሌላ ፍጆታ የሚውል ትክክለኛ የውጭ ሀገር ብር ምንዛሬ በሀገሪቱ ባንኮች ውስጥ የሌለ ከመሆኑም ባሻገር መጠባበቂያ ተብሎ የሚቀመጠው ገንዘብም ለጦር መሣሪያ መግዣ ተብሎ በባለስልጣናቱ እንደተወሰደ እነዚሁ የብሔራዊ ባንክ ምንጮች አጋልጠዋል።

በኑሮ ውድነቱ፣ በረሀቡ፣ በወያኔ እንግልት የተሰቃየው ሕዝብ ስለ እለት ጉርስ በሚያስበበት ጊዜ ዘራፊዎች ተጨማሪ የራስ ምታት እንደሆኑበትም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ያስረዳሉ፡፡

ሰሞኑን በአዲስ አበባና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች የደረሱን ዘገባዎች እንደሚያስረዱት ከሆነ ወያኔ ባመጣው ቀውስ ምክንያት የዕለት ጉርስ የተቸገሩ ወጣቶች በቡድንና በተናጠል በመሆን ሕዝቡን ቀን በብርሀን ሌት በጭለማ እየዘረፉ እንደሚገኙ ገልጿል፡፡

በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ ላይ መብራቶች መጥፋት ተከትሎ ከምሽቱ 3 ሰዓት በኋላ እንደልብ መንቀሳቀስ የቆመ ሲሆን በዚህ አጋጣሚ የተገኘ ሁሉ የዘረፋው ተጠቂ እንደሚሆንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

በቅርቡ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ የስንዴ ወረፋ ለመያዝ በጠዋት ወደ ቀበሌ ያመሩት አንዲት እናትና ሴት ልጃቸው የዘራፊዎቹ ሲሳይ ከመሆቸውም በላይ ጨኸቷን ባሰማችው ልጃቸው ላይ ግድያ የፈፀሙባት ሲሆን ሀገሪቷ ስርዓት አልባ እየሆነች መሆኑን ያሳያሉ የሚሉም በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በምሬት ይገልፃሉ፡፡
ከአዲስ አበባ ውጭም በየመንገዱ ላይ ዘራፊዎች መሣሪያ ታጥቀው ዝርፊያ እያካሄዱ መሆኑ ወያኔ መቆጣጠር ያልቻለበት ደረጃ ላይ መድረሱን አመላካች ነው ሲሉም አንዳንድ የጥቃቱ ሰለባ ቤተሰቦች ይገልፃሉ፡፡